## ለመሆኑ ችግራችን ምንድነው?

## ለከት ማጣት፤ አቅጣጫ መሳት!

ለነገሩ ችግር የቤት ልጅ ነው ተብሏል ። ባዳ አይደለም፤ ቅርብ ነው፤ ባንፈልገውም ችክ-- አለቅም ያለን "ወዳጅ" ነው ማለት ነው ። ችግር እንዳለን በቅድሚያ ማወቁ ራሱ ትልቅ እርምጃ ነው ። በሽታውን የሚደብቅ ሐኪም አይገኝለትም የተባለውን ያስታውሷል ። ችግራችንን ካውቅን መድሐኒት ፍለጋው ይቀላል፤ ችግራችንን ከደበቅንና ራሳችንንን ማታለሉን ከመረጥን ደግሞ በሽታችን ጸንቶብን ያሽመደምደናል፤ በአያሌውም ይጎዳናል ።

ችግራችንን ለከት ማጣትና አቅጣጫ መሳት በሚል ማጠቃለል እንችላለን ። ለክት ማጣት አቅምንም አለማውቅ፤ራስንም ድለላ፤መጃጃልና መሞኘትን ያጠቃልላል ። ለክት ማጣት ትሁትነትንም መተው፤ በሕዝብ ላይ መታበይ፤ የሹም ዶሮ ነኝ ባይነትን፤ በጠራራ ጸሀይ መዋሸትንም ይመለከታል ። በቅርቡ በአንድ ሩቅ ሀገር መለስተኛ ከተማ የሚኖሩ የተወስኑ ኢትዮጵያውያን አንድን ዜጋ ዳግማዊ አሉላ አባ ነጋ ብለው ሰየሙ ሸለሙ የሚል ዜና አሰሙን ። ከዛሬ ስንት ዓመት በፊት በአሜሪካ--ግለሰቧ አሁን እንኳን ከወያኔ ሰምራ ኑሮዋ በጎንደር-አዘዞ ነው-- ስፔንሰር የተባለ ፈረንጅን ሊቀመኳስ ብላ ሾማ ነበር። በምንና ማን በሰጣት ስልጣን? በምን ልክ? የወያኔ ቅጥረኛ የወር የማደናገሪያ እስረኛስ ማንዴላ ተብሎ አልነበር ? ሌላ መሪስ ጋንዲ፤ ኢየሱስ ወዘተ መባሉን ድሮ ይታተም የነበረው የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ነግሮን አልነበር? ለከት ማጣት ስንል ልክን ማጣት ሆነና አስመሳዩን ሀቀኛ፤ ያልተፈተነውን ጽኑ፤ ጠባቡን ሀገር ወዳድ፤ ቡከኑን የጦር መሪ ማለቱ ሰፍኖ የሕዝብ ጎራ ውጥንቅጡ ወጥቷል ቢባል ስህተት አይሆንም ። የዚህ ሁሉ ዋናው ችግርና ጉዳት የሕዝብ ትግል መሪ ተብለው የሚሞገሱት የታገሉና የሚታገሉት ሳይሆኑ፤ መስዋዕትነትን የሚቀበሉት ሳይሆኑ አስመሳዮችና የሀገራችን ሰው እንደሚለው የመንደር አውደልዳዮች መሆናቸው ነው ። በፖለቲካው መድረክም ዋና ሰባኪና አስተማሪ ነን ብለው የተሰየሙት እንቶኔ ተብዬዎች በአብዛኛ እምባጮዎች ናቸው። ግን የባዕዳን መሳሪያ ናቸውና ገንዘቡም መድረኩም በእጃቸው ነው ። ወደ ፖለቲካ መድረክ በ1997 መጣሁ የሚለው ለዘመናት የታገሉትን መካሪ ሳይሆን አልፎ ተርፎ ተቺና ዘላፊ ሆኖ አባማዬን ያቅራራል ። የደርግ ካድሬ፤ ባሰማያዊ ልብስና ሸጉጥ ታጣቂ የነበረው የዩኒቨርስቲ አስተማሪ ተሳስቼ ነበር ይቅርታን ሳያሰማ ያን

የታገለውን ትውልድ ነጋ ጠባ ይቀጠቅጣል ። ከወደ ሰማይ ድጋፍ አለን የሚሉም አሉ ። ትላንት ወያኔ ሆነው ስንት በደልና ግፍ የፈጸሙትን ጭምብል አጥልቀው ስም ቀይረው ታጋይ በሉን እያሉ ነው ። ስም መጥቀሱ አያሻም እንጂ እነ እግሌ ማለቱ ቀላል ነው ። ታጋይ ሴት አርአያ የሚባሉት ወጣት ዕድሜያቸውን በከተማና ገጠር ትግል ያጠፉትና  ለአመታት ደብዛቸው የጠፋው እነ አበራሽ በርታ ሳይሆኑ ከወያኔ ጋር ላንጣላ ተቆራኝተናል የሚሉት ናቸው። ዛሬ አሜሪካ እያሰለጠነና እያዘጋጃቸው ያለው ።

ሀገር አድን ትግል የሕዝብ ግዳጅ ነው ። ሕዝብ ያልተሳተፈበት ትግል ድልን ሊቀዳጅ አይችልም። የሕዝብን ሚናና ቦታ ድርጅትም ሆነ ግለሰቦች ሊቀሙ ከተነሱ ውጤቱ አያምርም ። በአሁኑ ጊዜ ራሳቸውን ምሁር ልሂቅና ዶክተር ፕሮፌሰር ያሉና ያውም በአብዛኛው በባዕድ ሀገር የሚኖሩ የሕዝብን ሚና፤ ቦታና ድምጽም ቀምተው ይውገረገራሉ ። ይህ ሌላ መጥፎ ችግር ሆኖ ይገኛል ። በሕዝባ ላይ የሚታበዩት እነዚህ ጉዶች ደግሞ ጉዳታቸው አስከፊ የሚሆነው ቃላቸውና ተግባራቸው ሆድና ጀርባ ከመሆናቸው ሌላ ከመታገል ይልቅ የሚታገሉትን ማጥቃትና ማደናቀፍ ዋናው ሚናቸው መሆኑ ነው ። ለከት አልባ   ተሁኗል። ስለዚህም   ፉክክሩና መጠላለፉ ደርቷል ። ወያኔንና ዘረኘነቱን ወይም አረመኔነቱን ማውገዙ ፋይዳ ቢስ ነው-- ወያኔ ከወያኔነቱ ጸረ ኢትዮጵያነቱ መላቀቅ የሚችል አይደለምና ። ችግር ስንል የራሳችንን ድክመትና ስህተት ላይ ማተኮሩ ነው ዋናው ስራችን መሆን ያለበት ። ዜጎችም ነጋ ጠባ ሊሞኙና ሊታለሉ ዝግጁ መሆን የለባቸውም ። አስመሳዩንና ቡከኑን ማወቅ አለባቸው ። ትላንት ያሞኛቸው ዛሬም ሊያጃጅላቸው ሲሞክር ወግድ በማለት ፈንታ ሰለባ ከሆኑለት ነገር ሁሉ ተበላሽ ማለት ነው :: ለሚከተለው ጉዳትም ሀላፊነቱ የነሱ ይሆናል ። ፖለቲካ ማንም ይዞ የሚሾፍረው መኪና፤ ማንም ከመ ቲያትር ዘፈን ይዞ የሚፈነጭበት ጉዳይ አይደለም ። አደብ ያልገዙ ግብዞችና ፖለቲካ ንግድ የመሰላቸው ቧልተኞች የሚጫወቱበትም መድረክ አይደለም ። የስደት መንግስት፤ የሽግግር መንግስት፤ በዚህ በዚያ ህብረት በሚል እየተካሄደ ያለውን አሳፋሪ ጫጫታ እየሰማን እያየን ነው ። ተቃዋሚውን ጎራ መሳቂያ መሳለቂያ ያደረጉ ሂደቶችና ያውም ደካማ እንቅስቃሴዎች። ለከት አልባ ከንቱ የራስ ውዳሴ ስምሪት ። ራስ ሳይጠና ጉተና ፤አንበሳ ሳይገድሉ ጉትቻ :፤

ለከት ማጣት፤ ልክን መሳት ትልቁ ችግርና ጉዳት ሆኖ ሲያደናቅፈን መክረሙ የሚታወቅ ነው ። የዚህ ውጤቱ አቅጣጫን መሳት ሆኖ የባሰ ጉዳትም ተከትሎ ለወያኔ መጥቀሙ ችግር መሆኑ የሚካድ አይደለም ። ገና ያኔ ወያኔ ኢሕአዴግ ነኝ ሲል የተሞኙለት ጥቂት አልነበሩም ። ወያኔ በባዕዳን እርዳታም ወደ ስልጣን ሲጓዝ ለንደን ድረስ ሄደው እነ እንድርያስ እሸቴ፤ አብዱል አባቦራ፡ ፕሮፌሰር መስፍን የሰጡትን ድጋፍም አንረሳውም። ፕሮፌሰሩ እነ መለስን ልጆቼ ብለው አሞካሽተው ለኢትዮጵያ

የቆመውን ኢዴኅቅን ደም የጠማው ብለው ማውገዛቸውን የምንረሳው አይደለም ። ከዚያም ሽግግር ባለው ጸረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴው ያጀቡትንም ማስታወስ እንችላለን ። ከወያኔ ተባብረው ለሀገር ግንጠላ ተባባሪ ሆነዋል ። ለጥቆም ሰላማዊ ትግል ብቻ፤ ሕዝብ ጦርነት ሰለቸው በሚል ልፈፋና አልፎም ትጥቅ ትግል ያሉትን ከዱላ መላ ይሻላል ብለው እያወገዙ ለወያኔ ጠቅመዋል ። እየጠቀሙም ናቸው ። አቅጣጫ መሳቱ የከፋ ደረጃ በመድረሱ ወያኔ ራሱ ጠላት መሆኑ ሁሉ በጥያቄ ገብቶ ነጋ ጠባ ዕርቅ፡ ጥሪን እንጂ፤ በሚል ደብዳቤ ለወያኔ፤ ምለላው አላቋረጠም ። ወያኔን አቅፎ ደግፎ ያለው አሜሪካ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ሀይል ልመናና ምስጋና (ለምን ይሆን?) ቀጥሏል ። ይህ ሀይል መልምሎ ያሰማራብንን አስመሳይ ተቃዋሚዎችንም አጋልጦ ከማባረር ፈንታ አንቱ ብሎ ማቀፉ ሰፍኗል ። ይህ ሌላ ችግራችን ነው ። የሀገራችን ሰው ድምቢጥ ሁሉ በየዛፉ ሲንጫጫ ሙዚቃ አይሰማም ባለው መሰረት ዛሬ ብዙዎች በየራሳቸው ስብስብ ነን እያሉ ተነጣጥለው በእኔ እበልጥ ፉክክር ሲናከሱ እያየን ነው። ተጠቃሚ ማን? ወያኔ ብቻ!

አቅጣጫ የሳትንበትና እድልም ያመለጠን ጊዜ ብዙ ነው ። ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ ሲል ይህ ዘረኛ ቡድን ኢትዮጵያን ያጠቃል፤ ይጎዳል በሚል ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም ከደር አይብስብንም ብሎ የተዘናጋ ዜጋ ቁጥር ብዙ ነበር ። ወያኔ በኢሕአፓ ላይ ተረማምዶና ስንቱን የሀገር ተስፋ ገድሎ ለስልጣን ሲበቃ በማውገዝ ፈንታ ያጀቡትና ያወደሱት ብዙ ናቸው ። ተማሪዎች ወያነ ስልጣን መያዙን ተቃውመው ሲሰልፉና ሲገደሉም ትግላቸውን ያጀበ አልነበረም ። በመገናገርና በመነሳት ፈንታ ዝምታን በማቀፍ መደረግ ያለበትን ሀገር አድን ትግል አደናቅፈነዋል ። ሁሉም ሀይሎች ያልተገኙበት የሽግግር ጉባኤ ሊካሄድ አይችልም በማለት ፈንታ ለወያኔ ሰለባ ሆነው በቀደደላቸው ቦይ ከመፍሰሳቸው በላይ የወያኔ ጦር የስሽግግር መንግስቱ ጦር ይሁንም ብለው ደግፈው በራሳቸው ላይ ጥፋትን ጋብዘዋል ። ወያነ ሻዕቢያ የሸረቡት ግንጠላንም አጅበዋል ። ወያኔና ሻእቢያ ሲጋጩ ኢትዮጵያን ከወያኔ መዳፍ ለማላቀቅ የማይገኝ ዕድል ተገኝቶ እያለ ለወያኔ ድለላ ሰልባ የሆኑ ብዙዎች በወያኔ ላይ በነሳት ፈንታ ለወያኔ ጦርነት ጭዳ ሆነው አልቀዋል ። ከባድሜ መልስ ወደ መለስ ብለው ያሞኟቸውም ስቀውብናል ። በ1997ኡም ምርጫ ተቃዋሚዎች በኣስፈላጊው ደረጃ ተቀናጅተው አመርቂ ውጠትን ማስመዝገብ ሲችሉ ማእበጥ መኩራራት አየለና ህብረቱም ላላ፡ ውጤቱም አላማረ ። የሙት ከተማ አድማ ሊያመጣ የሚችለውን ትልቅ ለውጥም ሁለት ተቃዋሚ ነን ባይ ግለሰቦች ከአሜሪክና እንግሊዝ ጋር ሆነው አደናቀፉት ። ወያኔና አለቆቹን መለማመጥ ሰፈነና መስዋዕትነት ምጸት ሆነብን ። የወያኔን የውስጥቱንም ቀውስ ልንጠቀምበት ስንችል በተዛባ ግምገማ ነጉደን ወያኔ ራሱን እንዲከላከል እድል ሰጥተነዋል ። የአህያ ፍሪዳ የእባብ ለማዳ የለም የተባለውን ዘንግተን ። በቅርቡ በሙሲም ኢትዮጵያውያን እየተደረገ

ያለው ሰላማዊ ተቃውሞ በሁሉ ሕዝብ ድጋፍ የወያኔን ውድቀት ሊያመጣ ሆኖ ሳለ ዝምታውና ገለልተኛነቱ ለወያኔ አመችቶታል ። ይባስ ብሎ ወያኔ የአባይ ግድብ ብሎ ተነስቶ ከግብጽ ጋር ተጋፈጡልኝ፤ ገንዘብ አዋጡልኝ ሲል ሰለባ የሆኑ ጥቂቶች አይደሉም ። ነአ ጠባ ልወያነ ሰለባ! እስከመቸ? ብዙርዎች ይራሳችንን ድክመትና ችግር ማንሳት ክቶም አይፈልጉም። ምርምሩ፤ ግምገማውና ትችቱ ስድብ ይመስላቸዋል ። ሀቁ ግን የራሳችንን ችግርና ድክመት ሙሉ በሙሉ ካልመረመርን፤ ካላወቅን እርምት ማድረግ ኣልመቻላችንን ያሳየናል። ለም ማበር ኣቃተን? ለምንስ የትግላችን ጠሮች የትግሉ ሰባኪ እንዲሆኑ ፈቅድንላቸው? ለምንስ ጠላቶች ወዳጆች መሰሉን?ለምንስ ወያኔ ለዓመታት ሊጫወትብን ቻለ? እነማን ናቸው ተቃዋሚ ነን እያሉ ሀገር አድን ትግሉን የሚቃወሙ ?

ፖለቲካ  የወጀድ እርሻ አይደለም ። የጡረታ ጊዜ መዝናኛ ስምሪትም አይደለም ። መነገጃም ሊሆን አይገባውም ። የህዝብና የገርን የነገ ዕጣ የሚመለከት ነው ። የፈሪዎችም የጓዳ መፎከሪያ አለመሆኑም መታወቅ ያለበት ነው። የህዝብ ጎራ በዚህም በዚያ ጥቃት እየደረሰበት ነው። እየከፋፈሉ የሚያዳክሙት፤ ለወያኔ በሚጠቅም ድእረጃ የሚያደናግሩት አልተኙለትም።  ለከት አንጣ፤ አቅጣጫ አንሳት ዜጎች!!